በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

የካቲት 6 ቀን 2007ዓ.ም

## ነግበኔን እናስብ፣ በተናጠል እንዳንጠቃ እንተባበር።

ወያኔ በስልጣን ላይ በተቀመጠ ማግስት በአባላቱ ፍላጎትና ነፃ ተሳትፎ በዴሞክራሲያዊ አካሄድ የተደራጀውን ሕጋዊ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) እውቅና ሻረ።የአመራር አባላቱን በመግደል፣ በማሰር፣አፍኖ በመሰወርና ከስራ በማፈናቀል፣ ከ11ሚሊዮን ብር በላይ የአባላቱን ገንዘብ ከባንክ በመዝረፍ፣ የክልልና የዞንና ማዕከላዊ( አገር አቀፍ) ጽ/ቤቶችን በመውረር፣ በመውረስና በመመዝበር የሻቢያ ወኪል ለነበረው በዮሐንስ ሐጎስ ለሚመራው ተለጣፊ ቡድን እንዳስረከበ ይታወሳል።
ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ ሆነና ጥር 21 ቀን 2007 ዓ.ም ወያኔ ሰራሹ ምርጫ ቦርድ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት) እና መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትን(መኢአድ) ወያኔ በፓርቲዎቹ ውስጥ አሥርጎ ላስገባቸው ቅጥረኞች ለትግሥቱ አወልና ለእነ አበባው መሐሪ እውቅና መስጠቱ ሥርዓቱ ጸረ ነፃ ድርጅትና ጸረ-መደበለ ፓርቲና ጸረ-ዲሞክራሲ እንደሆነ በገሃድ ያስመሰከረበት ሁኔታ ነው።ሥርዓቱ ለማይቆጣጠረው ተቃዋሚ ድርጅት እውቅና እንደማይሰጥ የፀረ-ድርጅት ታሪኩ በጉልህ ያስረዳል። ምርጫ ቦርድም ፈቃድ የሚሰጠው በድርጅቶች ውስጥ የሥርዓቱ ታማኝ ሰዎች መኖራቸውንና የአመራር ቦታዎችን መያዛቸውን ሲያረጋግጥ እንደሆነ ታይቷል።በሌላም በኩል በዚህ ሂደትም ቅጥረኛ ድርጅቶችን በመፍጠር የሕዝቡን ትግል አሰናክሏል።ሰኔ 24 ቀን 1983 ዓ.ም በወያኔ ጋባዥነት ተጠርቶ በነበረው የድርጅቶች ተወካዮችና የተወሰኑ ግለሰቦች በተሰበሰቡት ኮንፍረንስ ላይ እንዳልሳተፍ ወያኔ የመግቢያ ቪዛ ከለከለኝ እያለ ከ1984ዓ.ም ጀምሮ ብሶት ሲያሰማ የነበረው " ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት( ብዴሕ) የተባለው ድርጅት" " መገንጠል የድርጅቶች እንጂ የሕዝብ ጥያቄ አይደለም " የሚሉና የመሳሳሉትን የሕዝብ ስሜት የሚኮረኩሩ መፈክሮችን እያነሳ ጽ/ቤት ከፍቶ በየአደራሾቹ ስብሰባ ማካሄድ፣ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት ----- የሚያስችለው ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። በአንፃሩ በዚያን ወቅት ኢመማ በራሱ ጽ/ቤት እንኳ አባላቱን እንዳይሰበስብ ክልከላና ወከባው የከፋ ሆኖበት ነበር። ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት(ብዴሕ) የኢትዮጵያ ስም የሌላው ድርጅት ባገኘው አጋጣሚ ሐቀኛ ዜጎችን ስም ዝርዝር ለአሠማራው ግፈኛ ቡድን በማስረከብ ብዙዎቹች እንዲገደሉ፣ እንዲታሰሩ፣ እንዲታፈኑና በአጠቃላይም መጠነ ሰፊ አደጋ እንዲደርስ አድርጓል።በሌሎች ድርጅቶችም እንዲሁ ሰላዮችን አስርጓል። በሲቪክና በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የሚታየው ትርምስ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቀጠለ ክስተት እንደሆነ ልብ ይሏል።ከዚሁ ጋርም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና አንድነት ለመናድ ፍላጎት ያላቸው የውጭ መንግሥታትም ተላላኪ የሆኑ ግለሰቦችን በየድርጅቶች ውስጥ እያስገቡ የሕዝብን ትግል እያወሳሰቡትም እንደሆነ መዘንጋት የለበትም።
ዋነኛው ችግር ግን አንዱ ከሌላው ተመክሮ ያለመውሰድና ከስህተት ተምሮ ወዳጅ ጠላትን ለይቶ በጋራ ለመንቀሳቀስና ከግብ ለመድረስ ካለመስራት ላይ ነው።ሲቪል ማህበራትም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊያተኩሩበትና ሊረባረቡበት የሚገባው ተግባር ይህ መሆን እንዳለበት መገንዘብ **የቅድሚያ ቅድሚያ** ሊሰጠው ይገባል።
ዴሞክረሲያዊ ሥርዓት በአገሪቱ እንዲመሰረትና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ የሚታገሉ ሐቀኛ የሲቪል ማህበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች መተጋገዝ ይጠበቅባቸዋል። ነገበኔን እናስብ፣ በተናጠል እንዳንጠቃ እንተባበር። የአንደኛው አካል ጥቃት የሌላኛው እንደሆነ ተደርጎ ሊሰማ የግድ ነው። ወያኔ በጋምቤላ አኙዋኮች ላይ የፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል በአገሪቱ በሁሉም ስፍራ በሌሎች ዜጎች ላይ እንደተፈጸመ የሚቆጠር ነው። በአርባጉጉና በበደኖ ፣ በጌድዮ ፣ በሀዲያ፣ በአዋሳ፣ በአንዋር መስጊድ፣ በአደባባይ ኢየሱስ፣ በወላይታ፣ በሱማሊያ፣ በኦሮሞ፣ በባሕርዳር፣ በጎንደር---ወዘተ የተጨፈጨፉ ዜጎች በሁሉም ኢትዮጵያውያን ላይ የተነጣጠረ የጥቃት አካል ነው።



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*በደቡብ የአገሪቱ ክፍል ሰፍረው ለዘመናት የኖሩ ዜጎች የመብት ጥያቄ በማቅረባቸው ብቻ ከሚኖሩበት ቀዬ ተፈናቅለዋል፣ የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት እስር ቤት ተወርውረዋል።ሐሳባቸውን በነፃ ለመግለጽ የተነፈጉ ጋዜጠኞች በሐሰት ውንጀላ በሽብርተኝነት ተከሰው ለእስራት ተደርገዋል።በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ቆርጠው  የፖለቲካ ድርጅቶች መሪ የነበሩ እንዲሁ በፖለቲካ ከንፍነት የተዋቀረው ፍርድ ቤት ተብዬ ወስኖባቸው በወይኒ  ይማቅቃሉ።ይህን ሁሉ ግፍ ተሸክመን ወገኖቻችንን ለግድያ፣ለእስራት ፣ለሰደት፣  ለስቃይ---- አጋልጠን የመቀጠል ባሕል ማከታም አለበት።ለዜጎች ሁሉ ማንኛውንም  የትግል ስልት መቀበልና ተሳትፎ ማድረግም የወቅቱ አንገብጋቢ ጥሪ ሆኖ ቀርቧል።*

*ከዚሁ  ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላ ዋነኛ ጉዳይ በዚህ ወቅት በኢትዮጵያውያን ላይ ወያኔ እያደረሰ ያለውን ግፍና ሰቆቃ ላካቴው ለማቆም የውጭ ባእድ መንግሥታት ወይም አካላት የወሳኝነት ሚና የሚጠበቅ ሊሆን አይገባውም። ራሳችንን ነፃ ለማውጣት  ከራስችን በላይ ማንም የለም።በቅርቡ በአፍሪካ የአንድ  አገር ሕዝብ አምባገነኑን ሥርዓት በማስወገድ ታሪካዊና ታላቅ ድል አስመዝግቧል። እኛ ኢትዮጵያውያን በአይበገሬነትና በአርበኝነት ገድላችን ቅኝ ገዢዎችን ከምድራችን ጠራርገን እንዳስወጠን እየዘከርን ከውስጣችን ለበቀሉ የዘር መድሎ አቀንቃኞችና(Apartheid) አምባገነኖችን ማንበርከክ አለመቻላችን ጉዳይ በአንክሮ ሊጤን  የሚገባው  ነው።*

*በመጨረሻም  ወያኔ/ኢህአዴግ   በኢመማና በሌሎችም ሐቀኛ ድርጅቶች ላይ እየፈጸመ ያለውን የማፍረስ እርምጃ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በዚህ ሥርዓት የሲቪል ማህበራት ህልውናና የመድለ ፓርቲ ሥርዓት ዕውን ይሆናል ተብሎ ሰለማይጠበቅ ሲቪል ማህበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች ራሳቸውን ከሰላዮች አጽድተው ጠንካራ ሕብረት በመፍጠር ትግላቸውን እንዲያጎለብቱ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ እያሳሰበ  ከሰሞኑ ወያኔ በአንድነትና በመኢአድ ላይ የወሰደውን የፖለቲካ እርምጃ በጥብቅ ያወግዛል።*

*ሕዝባዊ አመጽ ይፋፋም!!*

*ዳር ተመልካችነት ያብቃ!!*

*ጀግኖችን ጭዳ አናስደርግ፣ ከጎናቸው እንቁም!!*